የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

--------ዓመት ቁጥር ----

አዲስ አበባ ---፪ሺ፲፫---- ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

---------- year No -----------


**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፸፪/፪ሺ፲፫**


**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የክፍል ከተማዎች እና ወረዳዎች እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፸፪/፪ሺ፲፫**

……………………..…………ገጽ------


**CONTENT**

**PROCLAMATION NO.72/2021**


**THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT SUB-CITIES AND 'WOREDAS' RE-ESTABLISHMENT PROCLAMATION NO.72/2021**…………………………page-----


## አዋጅ ቁጥር ፸፪/፪ሺ፲፫

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የክፍል ከተማዎች እና ወረዳዎች እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ

የነዋሪዎችን ብዛት በማመጣጠን፣ የአገልግሎት ተደራሽነትንና የማስተዳደር አቅምን ከግምት በማስገባት እያንዳንዱ ክፍል ከተማ ባልተማከለ የሥልጣን ክፍፍል መርህ በተሰጠው የቦታ ክልል ማዘጋጃ ቤት በመሆንና ከከተማው ማዕከል ጋር በመቀናጀት አገልግሎት እንዲሰጥና ወረዳዎችን እንዲያስተዳድር ለማድረግ የሚያስችለው ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት አደረጃጀት እንዲኖረው በማስፈለጉ ፤

የከተማ ማዕከላት በተዋረድ እንዲለሙ በማድረግ ለከተማው ነዋሪዎች ሚዛናዊ በሆነ ርቀትና ተደራሽ በሆነ መልኩ የአገልግሎት አቅርቦት እንዲመቻች


**የአንዱ ዋጋ**
**Unit price**


## PROCLAMATION NO.72/2021

## THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT SUB-CITIES AND 'WOREDAS' RE-ESTABLISHMENT PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has been found necessary to establish each sub-cities, being structured as a municipal within its demarcation, by considering the number of residents and its service rendering and administration capacity pursuant to the principles of decentralization that enables it to integrate with the central organs of the city and direct woredas having a transparent and accountable organization;

**WHEREAS,** it has been found necessary to ensure the existence of a just, efficient, effective and better city administration which is needed by the city


አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

ማድረግና የከተማ ነዋሪዎች የሚፈልጉትን ፍትሀዊ፣ ቀልጣፋና ብቁ የሆነ መልካም የከተማ አስተዳደር ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ይህንንም ለማሳካት እንዲቻል፣ በማስፋፊያ አካባቢ የሚገኙትን ክፍለ ከተማዎች እንደአግባቡ በመክፈልና በተወሰነ ሁኔታ ደግሞ ወረዳዎችን ወደ አዋሳኝ ክፍለ ከተማዎች እንደሁኔታው በማካተት እንደገና ማዋቀር አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተራ ፊደል (ሠ) ፤ አንቀጽ ፴፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና አንቀጽ ፴፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

residents through causing the progressive development of the city centers and facilitating the accessibility of the service provision within a reachable distance for the residents;

**WHEREAS,** it has been found necessary to relevantly divide the sub-cities that are found adjacent to expansion areas and, in some cases, to include and re-organize woredas to neighboring sub-cities, as may be necessary;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with letter (e) of sub-Article (2) of Article 11, Sub-Article (2) of Article 31 and Sub-Article (2) of Article 38 of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 361/2003 (as amended), the Addis Ababa City Council has issued this Proclamation as follows.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩) አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ " የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የክፍለ ከተማዎች እና ወረዳዎች እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፸፪/፪ሺ፲፫ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪) ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩) **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪) **"የከተማ አስተዳደር "** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫) **"ከንቲባ"** ማለት የከተማ ከንቲባ ነው፤

፬) **"ካቢኔ"** ማለት የከተማ ካቢኔ ነው፤

፭) **"ምክር ቤት"** ማለት የከተማ ምክር ቤት ነው፤

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as: "**The Addis Ababa City Government Sub-Cities and 'Woredas' Re-Establishment Proclamation No.72/2021.**"

2. **Definition**

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1. **"City"** means the Addis Ababa city;
2. **"City Government"** means the Addis Ababa City Government;
3. **"Mayor"** means the Mayor of the city;
4. **"Cabinet"** means the cabinet of the city;
5. **"Council"** means the council of the city;

፮) **"ክፍለ ከተማ "** ማለት የከተማው ሁለተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፤

፯) **"ወረዳ"** ማለት የከተማው ሶስተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን የሆነ የክፍለ ከተማ አካል ነው፤

፰) **"ቻርተር አዋጅ"** ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) ነው፤

፱) **"ቋሚ ኮሚቴ"** ማለት በቻርተር አዋጁ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተራ ፊደል (ሐ) ወይም ንዑስ አንቀጽ (፫) ተራ ፊደል (ሐ) የተጠቀሰው የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳ አስፈጻሚ አካል ነው፤

፲) **"አዋጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ (እንደተሻሻለ) ነው፤

፲፩) **"አዲስ ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ "** ማለት እንደአግባቡ በዚህ አዋጅ፡-

ሀ) አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ተ) የተቋቋመው ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ነው፤

ለ) ነባር ወረዳ ተከፍሎ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ወረዳ ፤

ሐ) ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ነባር ወረዳዎች ተቀላቅለው አንድ የሆነ ወረዳ ሲሆን ነው፤

፲፪) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

6. **"Sub-City"** means the second administrative stratum of the city;
7. **"Woreda"** means the third administrative stratum of the city, which is part of a sub-city;
8. **"Charter Proclamation"** means the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 361/2003 (as amended);
9. **"Standing Committee"** means the executive organ of the sub-city or woreda that is stated under letter (c) of Sub-Article (2) or letter (c) of Sub-Article (3) of Article 10 of the charter Proclamation;
10. **"Proclamation"** means the Addis Ababa city government executive organs re-establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 64/2019 (as amended);
11. **"New Sub-city or Woreda"** means as per the context, in this Proclamation:
    A. Lemi-Kura sub-city which is established according to letter (k) of Sub-Article (1) of Article (3);
    B. when the existing woreda is divided and becomes two or more woredas;
    C. when two or more existing woredas are merged and become one;
12. **"Person"** means any natural or juridical person.

## ክፍል ሁለት

## የክፍለ ከተማዎች እና ወረዳዎች አወቃቀር ማሻሻያ እና ተዛማጅ ሁኔታዎች

### ፫. የክፍለ ከተማዎች መቋቋም ፣ ኃላፊነት እና አሰራር ምንጭ

፩) የሚከተሉት ክፍለ ከተማዎች ሕጋዊ ሰውነት በማግኘት እንደገና ተቋቁመዋል፡-

ሀ) አራዳ ክፍለ ከተማ፤

ለ) ልደታ ክፍለ ከተማ፤

ሐ) ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፤

መ) አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ

ሠ) ኮልፌ-ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ፤

ረ) አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ፤

ሰ) ቦሌ ክፍለ ከተማ፤

ሸ) ጉለሌ ክፍለ ከተማ ፤

ቀ) ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ፤

በ) የካ ክፍለ ከተማ፤እና

ተ) ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ፤

፪) የእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነት፣ ስልጣን እና ተግባር እንዲሁም ሌሎች የአሰራር ሁኔታዎች በቻርተር አዋጁ እና በከተማው ምክር ቤት ሕግ መሠረት ይሆናል፤

፫) የእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ መጠሪያ ስም በከተማው ካቢኔ በሚወጣ ደንብ ሊለወጥ ወይም ሊሻሻል ይችላል፡፡

### ፬. የወረዳዎች መቋቋም፣ ኃላፊነት እና አሰራር ምንጭ

፩) የዚህ አዋጅ አካል ሆኖ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው አባሪ የተመለከቱት ፩፻፳ (አንድ መቶ ሃያ) ወረዳዎች ሕጋዊ ሰውነት በማግኘት እንደገና ተቋቁመዋል፤

## PART TWO

## AMENDMENT OF SUB-CITIES AND 'WOREDAS' ORGANIZATIONAL STRUCTURE AND RELATED MATTERS

### 3. Establishment of Sub-Cities, Source of Responsibility and Procedures

1. the following sub-cities are re-established having a juridical personality:
   A. Arada sub-city;
   B. Lideta sub-city;
   C. Kirkos sub-city;
   D. Addis Ketema sub-city;
   E. Kolife Keraniyo sub-city;
   F. Akaki Kaliti sub-city;
   G. Bole sub-city;
   H. Gullele sub-city;
   I. Nifas Silik Lafto sub-city;
   J. Yeka sub-city; and
   K. Lemi Kura sub-city.

2. The accountability, power and duties as well as other procedures of the administration of each sub-city shall be under the laws of the city council and with that of the charter Proclamation.

3. The name of each sub-city might be changed or amended through a Regulation to be issued by the city cabinet.

### 4. Establishment of Woredas, Source of Responsibility and Procedures

1. As indicated under the schedule attached with this Proclamation, the 120 (one hundred twenty) woredas shall be re-established having a juridical personality.

፪) የእያንዳንዱ ወረዳ አስተዳደር ተጠሪነት ለወረዳው ነዋሪዎችና ወረዳው ለሚገኝበት ክፍለ ከተማ አስተዳደር ሆኖ፡-

ሀ) እያንዳንዱ ወረዳ በቻርተር አዋጁ የተመለከተው የቀበሌ ስልጣን እና ተግባር፣ አደረጃጀት እንዲሁም ሌሎች የአሰራር ሁኔታዎች ይኖሩታል፤ ዝርዝሩ በከተማው ምክር ቤት ሕግ መሰረት የሚወሰን ይሆናል፤

ለ) የእያንዳንዱ ወረዳ መጠሪያ ስም በከተማው ካቢኔ በሚወጣ ደንብ ሊለወጥ ወይም ሊሻሻል ይችላል፡፡

፭.የወረዳ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

እያንዳንዱ የወረዳ ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) በወረዳው ዕቅድና የበጀት ፍላጎት ላይ በመምከር ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት እንዲቀርብ ያደርጋል፤

፪) የምክር ቤቱን አፈ-ጉባዔ፣ ጸሐፊ፣ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ይመርጣል፤

፫) ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ወይም ከምክር ቤት አባላት ውጭ ይመርጣል፤

፬) በወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቅራቢነት የወረዳን የቋሚ ኮሚቴ አባላት ሹመት ያጸድቃል፤

፭) በክፍለ ከተማው የሚመደብለትን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋሉን ያረጋግጣል፤

፮) የወረዳ ምክር ቤት ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፤

2. the administration of each woreda, being accountable to the residents of the woreda and the administration of the sub-city it exists:

   A. Every woreda shall have the power and duties, establishment as well as other procedures of a 'kebele' that is specified under the Charter Proclamation; the details shall be specified as per the laws of the city council.

   B. the name of each woreda might be changed or amended through a Regulation to be issued by the city cabinet.

**5. Power and Duties of the Woreda' Council**

The council of each woreda shall have the following power and duties:

1. discuss the plan and budget of the woreda and cause the presentation of same to the council of the sub-city;
2. elect a spokesperson, secretary and chief executive officer for the council among its members;
3. elect the deputy chief executive officer among the members of the council or out of its members;
4. approve the appointment of members of the standing committees of the woreda through the nomination of the thereof by the chief executive officer of the woreda;
5. make sure that the allocated budget for the woreda administration by the sub-city is properly utilized;
6. establish standing committees for the woreda council

፯) ከወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዓመታዊና ወቅታዊ ሪፖርት ይቀበላል፣ መርምሮም ውሳኔ ይሰጣል፣

፰) ስለአሰራሩ የሚወስን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፡፡

**፮. የወረዳ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ**

፩) ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ሆኖ የአፈ-ጉባዔው የስራ ዘመን የምክር ቤቱ የስራ ዘመን ይሆናል፣ ሥራውን በፈቃዱ ሲለቅ ወይም በምክር ቤቱ ከኃላፊነቱ ሲታገድ ወይም የምክር ቤት አባልነቱ ሲቋረጥ ከኃላፊነቱ ሊሰናበት ይችላል፣

፪) የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት ያደራጃል፣ ይመራል፣

፫) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ምክር ቤቱን ይወክላል፣

፬) የምክር ቤቱን ስብሰባ ይጠራል፣ ይመራል፣ የምክር ቤቱን ኮሚቴዎች ያስተባብራል፣

፭) የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣

፮) የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት ሠራተኞች አግባብ ባለው የመንግስት ሠራተኞች አስተዳር ሕግ መሠረት ያስተዳድራል፣

፯) ምክር ቤቱ በአባላቱ ላይ የሚወስዳቸውን የስነ-ሥረዓት እርምጃዎች ያስፈጽማል፣

፰) በምክር ቤቱ ስለሚወሰኑት ውሳኔዎች ወቅታዊ መግለጫ ለወረዳው ነዋሪዎች ይሰጣል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፣

፱) የምክር ቤቱን አባላት የአቅም ግንባታ ሥራ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በመቀናጀት ያስፈጽማል፣

፲) ከምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

7. receive annual and recent reports from the chief executive officer of the woreda; evaluate same and pass a decision;
8. issue its own rules of procedures.

**6. Spokesperson of the Woreda Council**

1. The spokesperson, being accountable to the council, his term in office shall be that of the council; he shall be dismissed from his responsibilities when he willingly resigns or removed from his responsibilities by the council or when his council membership is terminated;
2. lead the office of the council;
3. represent the council in its dealings with third parties;
4. call and preside over meetings of the council; coordinate the committees of the council;
5. prepare the budget of the office of the council; implement same upon approval;
6. manage the employees of the office of the council as per the civil servants' laws;
7. execute disciplinary measures taken by the council against its members;
8. provide latest announcements for the residents of the woreda regarding the decisions made by the council; notify same to the concerned organs;
9. prepare plans for the capacity building activities of the members of the council; implement same in collaboration with the relevant executive organs;
10. carry out other duties given by the council.

## ፯. የወረዳ ምክር ቤት ፀሐፊ

የምክር ቤቱ ፀሐፊ ተጠሪነቱ ለወረዳ አፈ-ጉባዔ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) ከአፈ-ጉባዔው ጋር በመመካከር የምክር ቤቱን አጀንዳ ያዘጋጃል፤ የምክር ቤቱን ቃለ ጉባዔ ይይዛል፤ ወይም እንዲያዝ ያደርጋል፤ አፈ-ጉባዔው በማይኖርበት ጊዜ አፈ-ጉባዔውን ተክቶት ይሰራል፤

፪) የምክር ቤቱና የምክር ቤቱ ኮሚቴዎች ቃለ-ጉባዔዎችና ሰነዶች እንዲያዙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፤ ቃለ-ጉባዔዎችን ያሰራጫል፤

፫) የምክር ቤቱ ፀሐፊ የስራ ዘመን የምክር ቤቱ የስራ ዘመን ይሆናል፤ ሆኖም ሥራውን በራሱ ፈቃድ ሲለቅ ወይም በምክር ቤቱ ከኃላፊነቱ ሲታገድ ወይም የምክር ቤት ኃላፊነቱ ሲቋረጥ ከኃላፊነቱ ሊሰናበት ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፰. የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩) በአዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፸፭ እና ፹፫ እንደቅደም ተከተላቸው የተደነገገው የክፍለ ከተማዎች እና የወረዳዎች ዝርዝር በዚህ አዋጅ ተሽሮ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ተተክቷል፤

፪) ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም የከተማው አስተዳደር አዋጅ ፣ መመሪያ ፣ ደንብ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 7. Secretary of the Woreda Council

The secretary of the council, being accountable to the spokesperson of the woreda, shall have the following power and duties:

1. prepare agendas for the council having a discussion with the spokesperson; maintain or cause the maintaining of the minute of the council; act on behalf of the spokesperson in his absence;
2. cause for the recording and safe keeping of the minutes and documents of the council and its committees;
3. the term of office of the secretary of the council shall be that of the council; however, he shall be dismissed from his responsibilities when he willingly resigns or removed from his responsibilities by the council or when his council membership is terminated.

## PART THREE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 8. Repealed and Inapplicable Laws

1. The list of sub-cities and woredas specified under Article 75 and 83, respectively, of Proclamation No. 64/2019 (as amended), is repealed by this Proclamation and replaced by the schedule which is attached with this Proclamation.
2. Any Proclamation, Regulation, directive or customary practices of the city government which is inconsistent with this Proclamation shall not be applicable in respect of matters covered under this Proclamation.

**፱. የመብት እና ግዴታ መተላለፍ**

፩) በአዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፸፭ እና ፹፫ መሰረት የተቋቋመ ክፍለ ከተማ የወሰን ማሻሻያ ቢኖርም ወይም ባይኖርም የነባሩ ክፍለ ከተማ መብትና ግዴታ ተላልፈውለታል፤

፪) የነባሩ ወረዳ መብትና ግዴታ በዚህ አዋጅ መሰረት ለተቋቋመ ወረዳ ተላልፏል፡፡

**፲. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

፩. በክፍለ ከተማና በወረዳ እንደየደረጃጃቸው ተቋቁመው የነበሩ የምክር ቤት አደረጃጀትና የምክር ቤት እንደራሲዎች የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ጊዜ እንዲራዘምና ቀጣዩ ምርጫ ስለሚካሄድበት ሁኔታ በወሰነው መሠረት በነበሩበት እንዲቀጥሉ፤

፪. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ጊዜ እንዲራዘምና ቀጣዩ ምርጫ ስለሚካሄድበት ሁኔታ በወሰነው መሰረት ምክር ቤቶች እስከሚደራጁ ድረስ በዚህ አዋጅ የተቋቋሙ አዲስ ክፍለ ከተማ እና አዲስ ወረዳዎች ምክር ቤት ስለማይኖሩዋቸው፡-

ሀ) የክፍለ ከተማዎቹና ወረዳዎቻቸው ጊዜያዊ አስተዳደሮች በከንቲባው ይደራጃሉ፤

ለ) የጊዜያዊ አስተዳደሮቹ ዋና ስራ አስፈጻሚዎች፣ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚዎች እና ቋሚ ኮሚቴዎቻቸው አባላት በከንቲባው ይሾማሉ፤

**9. Transfer of Rights and Obligations**

1. A sub-city which is established pursuant to Article 75 and 83 of Proclamation No.64/2019 (as amended), with or without the adjustment made on the boundary, the rights and obligations of the existing sub-city are transferred to the thereof.

2. The rights and obligations of the existing woreda are transferred to the woreda which is established by this proclamation.

**10. Transitory Provisions**

1. According to the decision made by the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia to extend the election period and the conditions to conduct the election, the already established organization of a council at the sub-city and woreda level and their officials shall remain functional;

2. According to the decision made by the House of Peoples' Representatives to extend the election period and the conditions to conduct the election, until the establishment of councils, as the new sub-cities and new woredas established under this Proclamation shall have no councils:

   A. the transitional administrations of the sub-cities and its woredas shall be established by the Mayor;

   B. the chief executive officers, the deputy chief executive officers and the members of the standing committees of the transitional administrations shall be appointed by the Mayor;

ሐ) የጊዜያዊ አስተዳደሮቹ ዋና ስራ አስፈጻሚዎች፣ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚዎች፣ እና ቋሚ ኮሚቴዎች እንደ አግባቡ በቻርተር እና በአዋጁ ለክፍለ ከተማ እና ለወረዳ ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ እና ቋሚ ኮሚቴ የተሰጡ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩዋቸዋል፤

መ) ጊዜያዊ አስተዳደሮቹ አስፈጻሚ አካሎቻቸውን ያደራጃሉ፣ አግባብ ባለው አካል በሚጸድቅላቸው መዋቅር መሰረት ሰራተኞችን ይቀጥራሉ ወይም ይመድባሉ፤ ያስተዳድራሉ፤ ያሰናብታሉ፤

፫. የክፍለ ከተማው አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተራ ፊደል (ሐ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባርና ይኖሩታል፣-

ሀ) የክፍለ ከተማውን ጊዜያዊ አስተዳደር ዕቅድ ያጸድቃል፤

ለ) ከከተማው ምክር ቤት የተመደበለትን በጀት ይደለድላል፤ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

ሐ) የክፍለ ከተማውን ጊዜያዊ አስተዳደር ዓመታዊና ወቅታዊ ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

፬. የወረዳው ጊዜያዊ አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተራ ፊደል (ሐ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፭) የተደነገጉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

C. the chief executive officers, the deputy chief executive officers and the standing committees of the transitional administrations shall have the power and duties of the chief executive officer, the deputy chief executive officer and the standing committee of the sub-city and woreda, respectively, which are stated under the Charter and the Proclamation;

D. the transitional administrations shall organize its executive organs; hire or assign, manage and dismiss employees as per the approval of the structure by the relevant organ;

3. without prejudice to letter (c) of Sub-Article (2) of this Article, the standing committee of the sub-city shall have the following power and duties:

A. approve the plan of the transitional administration of the sub-city;

B. distribute the budget which is allocated by the city council; ensure the proper utilization of the thereof;

C. examine the annual and current reports of the transitional administration of the sub-city and make a decision.

4. without prejudice to letter (c) of Sub-Article (2) of this Article, the standing committee of the transitional administration of the woreda shall have the power and duties stated under Sub-Article (1) and (5) of Article (5) of this Proclamation;

፭. በአዋጁ ተቋቁሞ የነበረ ማናቸውም የክፍለ ከተማ አስተዳደር ወይም የወረዳ አስተዳደር ለሁለት ከተከፈለ ወይም የወሰን ማሻሻያ ከተደረገበት በመከናወን ላይ ያሉ ያልተጠናቀቁ ስራዎችን እያከናወነ ለርክክብ ዝግጁ ያደርጋል፣ በከንቲባው በሚወሰነው ጊዜ እና ሁኔታ መሰረት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ እንደየአግባቡ ያስረክባል፣

፮. ወደ አዲሱ ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ ወይም የወሰን ማሻሻያ ወደ ተደረገበት ወረዳ በተከለሉ አካባቢዎች የሚኖሩ ነዋሪዎች የነዋሪነት መታወቂያ፣ የንግድ ምዝገባ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና ሌሎች ሰነዶች የአድራሻ ማስተካከያ እስኪደረግባቸው ድረስ በነበረው አሰራር አገልግሎታቸው ይቀጥላል፡፡

**፲፩. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፲ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፲ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ**

5. If any of the sub-city or woreda administration established under the proclamation is divided into two or its boundaries are modified, it shall continue to carry out activities that are not completed and make it ready for handover; deliver it to the sub-city or woreda respectively, established by this Proclamation according to the time and condition to be decided by the Mayor;
6. The residents living in areas where demarcated to the new sub-city or woreda or a woreda where a boundary improvement has been made, services regarding residence identity card, trade registration license, tax payer identification number and other documents shall remain in the existing system until address adjustments are made.

**11. <u>Effective Date</u>**

This proclamation shall enter into force as of the 20th day of October, 2020.

**Done at Addis Ababa, this 20th day of October 2020.**

**Adanech Abiebie**
**Deputy Mayor of Addis Ababa City**

# አባሪ 1

## የተሻሻለ የክፍለ ከተማዎች እና ወረዳዎች ዝርዝር ሰንጠረዥ

| የተሻሻለዉ ስያሜ | | ነባሩ የ2011 ስያሜ /አዋጅ ቁጥር 64/2011/ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| ክፍለ ከተማ | ወረዳ | የ2011 ክፍለ ከተማ | የ2011 ወረዳ | |
| አራዳ | 1 | አራዳ | 01 | የወሰን ማሻሻያ የተደረገበት |
| አራዳ | 2 | አራዳ | 02 እና 03 | ወ.2 ፣ ወ.3 እና ወ.5 በከፊል በአንድ የተጠቃለለ |
| አራዳ | 4 | አራዳ | 04 | |
| አራዳ | 5 | አራዳ | 05 እና 10 | ወ.10 እና ወ.5 በአንድ የተጠቃለለ |
| አራዳ | 6 | አራዳ | 06 | ከየካ ወ.4 በከፊል የተጨመረበት |
| አራዳ | 7 | አራዳ | 07 | ከወ.7 እና ወ-9 በከፊል የተጨመረበት |
| አራዳ | 8 | አራዳ | 08 | ከወ.9 በከፊል የተጨመረበት |
| አራዳ | 9 | አራዳ | 09 | ከወ.7 እና ወ-8 በከፊል የተጨመረበት |
| ልደታ | 1 | ልደታ | 01 | የወሰን ማሻሻያ የተደረገበት |
| ልደታ | 2 | ልደታ | 02 | |
| ልደታ | 3 | ልደታ | 03 እና 04 | ከወ.4 በከፊል የተጨመረበት |
| ልደታ | 4 | ን/ስ/ላ | 04 | ከንፋስ ስልክ ላፍቶ የመጣ |
| ልደታ | 5 | ልደታ | 05 እና 06 | ወ.5፣ ወ.6 እና ወ.9 በከፊል በአንድ የተቋቋመ |
| ልደታ | 6 | ን/ስ/ላ | 03 | ለሁለት የተከፈለና ከኮልፌ ወ.5 በከፊል የተጨመረበት |
| ልደታ | 7 | ልደታ | 07 እና 08 | ወ.7 እና ወ.8 የተጠቃለለና አከላለል ማስተካከያ ተደረገ |
| ልደታ | 8 | ን/ስ/ላ | 03 | ለሁለት የተከፈለና ከኮልፌ ወ.5 በከፊል የተጨመረበት |
| ልደታ | 9 | ልደታ | 04 እና 09 | ከወ.4 በከፊል የተጨመረበት |
| ልደታ | 10 | ልደታ | 10 | ከወ.1 በከፊል የተጨመረበት |

# Annex 1

## Schedule for the Revised Sub-Cities and ‘Woredas’ List

| Revised Name | | Existing Name in 2019 (Proc. No. 64/2019) | | Remark |
|---|---|---|---|---|
| Sub-City | Woreda | Name of the Sub-Cities | Name of the ‘Woreda’ in 2019 | |
| Arada | 1 | Arada | 01 | boundary improvement made |
| Arada | 2 | Arada | 02 and 03 | W.2, W.3 and W.5 partially merged as one |
| Arada | 4 | Arada | 04 | |
| Arada | 5 | Arada | 05 and 10 | W.10 and W.5 are merged as one |
| Arada | 6 | Arada | 06 | partially added from Yeka W.4 |
| Arada | 7 | Arada | 07 | partially added from W.7 and W.9 |
| Arada | 8 | Arada | 08 | partially added from W.9 |
| Arada | 9 | Arada | 09 | partially added from W.7 and W.8 |
| Lideta | 1 | Lideta | 01 | boundary improvement made |
| Lideta | 2 | Lideta | 02 | |
| Lideta | 3 | Lideta | 03 and 04 | partially added from W.4 |
| Lideta | 4 | Nifas Silik Lafto | 04 | taken from Nifas Silik Lafto |
| Lideta | 5 | Lideta | 05 and 06 | W.5, W.6 and W.9 partially established as one |
| Lideta | 6 | Nifas Silik Lafto | 03 | divided into two and partially added from W.5 of Kolife Keraniyo |
| Lideta | 7 | Lideta | 07 and 08 | W.7 and W.8 merged and demarcation adjustment made |
| Lideta | 8 | Nifas Silik Lafto | 03 | divided into two and partially added from W.5 of Kolife Keraniyo |
| Lideta | 9 | Lideta | 04 and 09 | partially added from W.4 |
| Lideta | 10 | Lideta | 10 | partially added from W.1 |

| የተሻሻለዉ ስያሜ | | ነባሩ የ2011 ስያሜ /አዋጅ ቁጥር 64/2011/ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| ክፍለ ከተማ | ወረዳ | የ2011 ክፍለ ከተማ | የ2011 ወረዳ | |
| ቂርቆስ | 1 | ቂርቆስ | 01 | ከወ-8 እና ከቦሌ ወ.4 በከፊል የተጨመረበት |
| ቂርቆስ | 2 | ቂርቆስ | 02 | ከወ.9 በከፊል የተጨመረበት |
| ቂርቆስ | 3 | ቂርቆስ | 03 | ከወ.2 በከፊል የተጨመረበት |
| ቂርቆስ | 4 | ቂርቆስ | 04 | ከወ.2 በከፊል የተጨመረበት |
| ቂርቆስ | 5 | ቂርቆስ | 05 እና 06 | ከወ.6 በከፊል የተጨመረበት |
| ቂርቆስ | 7 | ቂርቆስ | 07 | ከወ-6፣ ወ-9፣ ከልደታ ወ-8 እና ከአራዳ ወ-1 በከፊል የተጨመረበት |
| ቂርቆስ | 8 | ቂርቆስ | 08 | ከወ-1 በከፊል የተጨመረበት |
| ቂርቆስ | 9 | ቂርቆስ | 09 | ከወ-2 በከፊል የተጨመረበት |
| ቂርቆስ | 10 | ቂርቆስ | 6፣ 7 እና 11 | ከወ-6፣ ወ-7 እና ወ-11 በከፊል የተጨመረበት |
| ቂርቆስ | 11 | ቂርቆስ | 11፣10 እና 04 | ከወ-4 እናወ-10 በከፊል የተጨመረበት |
| አዲስ ከተማ | 1 | አዲስ ከተማ | 01 | |
| አዲስ ከተማ | 3 | አዲስ ከተማ | 02 እና 03 | ወ.2 በሙሉ የተጨመረበት |
| አዲስ ከተማ | 4 | አዲስ ከተማ | 04 | ከወ.3 በከፊል የተጨመረበት |
| አዲስ ከተማ | 5 | አዲስ ከተማ | 05 | የአከላለል ማሻሻያ የተደረገበት |
| አዲስ ከተማ | 6 | አዲስ ከተማ | 06 እና 07 | ከወ.7 እና ከወ.5 በከፊል የተጨመረበት |
| አዲስ ከተማ | 8 | አዲስ ከተማ | 08 | |
| አዲስ ከተማ | 9 | አዲስ ከተማ | 09 | ከወ.7 በከፊል የተጨመረበት |
| አዲስ ከተማ | 10 | አዲስ ከተማ | 10 | |

| Revised Name | | Existing Name in 2019 (Proc. No. 64/2019) | | Remark |
|---|---|---|---|---|
| Sub-City | Woreda | Name of the Sub-City in | Name of the 'Woreda in 2019 | |
| Kirkos | 1 | Kirkos | 01 | partially added from W.8 and W.4 of Bole |
| Kirkos | 2 | Kirkos | 02 | partially added from W.9 |
| Kirkos | 3 | Kirkos | 03 | partially added from W.2 |
| Kirkos | 4 | Kirkos | 04 | partially added from W.2 |
| Kirkos | 5 | Kirkos | 05 and 06 | partially added from W.6 |
| Kirkos | 7 | Kirkos | 07 | partially added from W.6, W.9, Lideta W.8 and Arada W.1 |
| Kirkos | 8 | Kirkos | 08 | partially added from W.1 |
| Kirkos | 9 | Kirkos | 09 | partially added from W.2 |
| Kirkos | 10 | Kirkos | 6,7 and 11 | partially added from W.6, W.7 and W.11 |
| Kirkos | 11 | Kirkos | 11,10 and 04 | partially added from W.4 and W.10 |
| Addis Ketema | 1 | Addis Ketema | 01 | |
| Addis Ketema | 3 | Addis Ketema | 02 and 03 | W.2 is fully added |
| Addis Ketema | 4 | Addis Ketema | 04 | partially added from W.3 |
| Addis Ketema | 5 | Addis Ketema | 05 | demarcation adjustment is made |
| Addis Ketema | 6 | Addis Ketema | 06 and 07 | partially added from W.7 and W.5 |
| Addis Ketema | 8 | Addis Ketema | 08 | |
| Addis Ketema | 9 | Addis Ketema | 09 | partially added from W.7 |
| Addis Ketema | 10 | Addis Ketema | 10 | |

| የተሻሻለዉ ስያሜ | | ነባሩ የ2011 ስያሜ /አዋጅ ቁጥር 64/2011/ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| ክፍለ ከተማ | ወረዳ | የ2011 ክፍለ ከተማ | የ2011 ወረዳ | |
| አዲስ ከተማ | 11 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 11 | ከኮልፌ ወ-8 በከፊል የተጨመረበት |
| አዲስ ከተማ | 12 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 12 እና 13 | ከኮልፌከ ወ-11 እና ከወ-13 በከፊል የተጨመረበት |
| አዲስ ከተማ | 13 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 13 | የአከላለል ማሻሻያ የተደረገበት |
| አዲስ ከተማ | 14 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 14 | |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 1 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 01 | ከን.ስ.ላፍቶ ወ.2 በከፊል የተጨመረበት |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 2 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 02 | ከን.ስ.ላፍቶ ወ.1 በከፊል የተጨመረበት |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 3 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 03 | ለሁለት የተከፈለዉ የተቋቋመ |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 4 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 04 | |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 5 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 05 | የአከላለል ማሻሻያ የተደረገበት |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 6 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 06 | |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 7 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 07 | ከወ.3 በከፊል የተጨመረበት |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 8 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 08 | ከወ.11 በከፊል የተጨመረበት |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 9 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 09 | የአከላለል ማሻሻያ የተደረገበት |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 10 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 10 | ከወ.9 በከፊል የተጨመረበት |
| ኮልፌ ቀራኒዮ | 11 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 03 | ከወ.3 ተከፍሎ የተቋቋመ |
| ቦሌ | 1 | ቦሌ | 01 | ከወ.12 እና ከወ.13 በከፊል የተጨመረበት |
| ቦሌ | 2 | ቦሌ | 02 | |
| ቦሌ | 3 | ቦሌ | 03 | የአከላለል ማሻሻያ የተደረገበት |
| ቦሌ | 4 | ቦሌ | 04 | ከወ.3 በከፊል የተጨመረበት |
| ቦሌ | 5 | ቦሌ | 05 | ከወ.3 እና ከወ.4 በከፊል የተጨመረበት |
| ቦሌ | 6 | ቦሌ | 06 | |
| ቦሌ | 7 | ቦሌ | 07 | |
| ቦሌ | 11 | ቦሌ | 11 | ለሁለት የተከፈለና ከወ.9 በከፊል የተጨመረበት |

| **Revised Name** | | **Existing Name in 2019 (Proc. No. 64/2019)** | | **Remark** |
|---|---|---|---|---|
| Sub-City | Woreda | Name of the Sub- | Name of the 'Woreda' | |
| Addis Ketema | 11 | Kolife Keraniyo | 11 | partially added from W.8 of Kolife Keraniyo |
| Addis Ketema | 12 | Kolife Keraniyo | 12 and 13 | partially added from w.11 and w.13 of Kolife Keraniyo |
| Addis Ketema | 13 | Kolife Keraniyo | 13 | demarcation adjustment is made |
| Addis Ketema | 14 | Kolife Keraniyo | 14 | |
| Kolife Keraniyo | 1 | Kolife Keraniyo | 01 | partially added from W.2 of Nifas Silik Lafto |
| Kolife Keraniyo | 2 | Kolife Keraniyo | 02 | partially added from W.1 of Nifas Silik Lafto |
| Kolife Keraniyo | 3 | Kolife Keraniyo | 03 | divided into two and established |
| Kolife Keraniyo | 4 | Kolife Keraniyo | 04 | |
| Kolife Keraniyo | 5 | Kolife Keraniyo | 05 | demarcation adjustment is made |
| Kolife Keraniyo | 6 | Kolife Keraniyo | 06 | |
| Kolife Keraniyo | 7 | Kolife Keraniyo | 07 | partially added from W.3 |
| Kolife Keraniyo | 8 | Kolife Keraniyo | 08 | partially added from W.11 |
| Kolife Keraniyo | 9 | Kolife Keraniyo | 09 | demarcation adjustment is made |
| Kolife Keraniyo | 10 | Kolife Keraniyo | 10 | partially added from W.9 |
| Kolife Keraniyo | 11 | Kolife Keraniyo | 03 | divided from W.3 and established |
| Bole | 1 | Bole | 01 | partially added from W.12 and W.13 |
| Bole | 2 | Bole | 02 | |
| Bole | 3 | Bole | 03 | demarcation adjustment is made |
| Bole | 4 | Bole | 04 | partially added from W.3 |
| Bole | 5 | Bole | 05 | partially added from W.3 and W.4 |
| Bole | 6 | Bole | 06 | |
| Bole | 7 | Bole | 07 | |
| Bole | 11 | Bole | 11 | divided into two and partially added from W.9 |

| የተሻሻለዉ ስያሜ | | ነባሩ የ2011 ስያሜ /አዋጅ ቁጥር 64/2011/ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| ክፍለ ከተማ | ወረዳ | የ2011 ክፍለ ከተማ | የ2011 ወረዳ | |
| ቦሌ | 12 | ቦሌ | 12 | የአከላለል ማሻሻያ የተደረገበት |
| ቦሌ | 13 | ቦሌ | 13 | የአከላለል ማሻሻያ የተደረገበት |
| ቦሌ | 14 | ቦሌ | 14 | |
| ለሚ ኩራ | 14 | የካ | 12 እና 13 | ከየካ ወ-12 ተካፍለዉና ከወ-13 በከፊል ተጨምሮ ተቋቋመ |
| ለሚ ኩራ | 2 | የካ | 13 | ከ ወ-13 ተከፍለዉ ተቋቋመ |
| ለሚ ኩራ | 3 | ቦሌ | 10 | ከቦሌ ወ-10 ተከፍለዉ አዲስ ተቋቋመ |
| ለሚ ኩራ | 4 | ቦሌ | 10 | ከቦሌ ወ-10 ተከፍለዉ አዲስ ተቋቋመ |
| ለሚ ኩራ | 5 | ቦሌ | 10 | ከቦሌ ወ-10 ተከፍለዉ አዲስ ተቋቋመ |
| ለሚ ኩራ | 6 | ቦሌ | 11 | ከ ወ-11 ለሁለት ተከፍሎ የተቋቋመ |
| ለሚ ኩራ | 8 | ቦሌ | 08 | |
| ለሚ ኩራ | 9 | ቦሌ | 09 | የአከላለል ማሻሻያ የተደረገበት |
| ለሚ ኩራ | 10 | ቦሌ | 10 | የአከላለል ማሻሻያ የተደረገበት |
| ለሚ ኩራ | 13 | የካ | 11 እና 13 | ለሁለት የተከፈለና ከየካ ወ.11 በከፊል የተጨመረበት |
| የካ | 1 | የካ | 01 | |
| የካ | 2 | የካ | 02 | |
| የካ | 3 | የካ | 03 | |
| የካ | 4 | የካ | 04 | ከጉለሌ ወ.2፣ ከአራዳ .ወ.7 በከፊል የተጨመረበት |
| የካ | 5 | የካ | 05 | የአከላለል ማሻሻያ የተደረገበት |
| የካ | 6 | የካ | 06 | ከወ.7 በከፊል የተጨመረበት |
| የካ | 7 | የካ | 07 | የአከላለል ማሻሻያ የተደረገበት |
| የካ | 8 | የካ | 08 | |
| የካ | 9 | የካ | 09 | ከወ.5 በከፊል የተጨመረበት |
| የካ | 10 | የካ | 10 | ከወ.5 በከፊል የተጨመረበት |

| Revised Name | | Existing Name in 2019 (Proc. No. 64/2019) | | Remark |
|---|---|---|---|---|
| Sub-City | Woreda | Name of the Sub-City in 2019 | Name of the 'Woreda' in 2019 | |
| Bole | 12 | Bole | 12 | demarcation adjustment is made |
| Bole | 13 | Bole | 13 | demarcation adjustment is made |
| Bole | 14 | Bole | 14 | |
| Lemi Kura | 14 | Yeka | 12 and 13 | divide from Yeka W.12 and partially added from W.13 and established |
| Lemi Kura | 2 | Yeka | 13 | divided from W.13 and established |
| Lemi Kura | 3 | Bole | 10 | divided from Bole W.10 and newly established |
| Lemi Kura | 4 | Bole | 10 | divided from Bole W.10 and newly established |
| Lemi Kura | 5 | Bole | 10 | divided from Bole W.10 and newly established |
| Lemi Kura | 6 | Bole | 11 | divided into two from W.11 and established |
| Lemi Kura | 8 | Bole | 08 | |
| Lemi Kura | 9 | Bole | 09 | demarcation adjustment is made |
| Lemi Kura | 10 | Bole | 10 | |
| Lemi Kura | 13 | Yeka | 11 and 13 | divided into two and partially added from W.11 from Yeka |
| Yeka | 1 | Yeka | 01 | |
| Yeka | 2 | Yeka | 02 | |
| Yeka | 3 | Yeka | 03 | |
| Yeka | 4 | Yeka | 04 | partially added from Gullele W.2 and Arada W.7 |
| Yeka | 5 | Yeka | 05 | demarcation adjustment is made |
| Yeka | 6 | Yeka | 06 | partially added from W.7 |
| Yeka | 7 | Yeka | 07 | demarcation adjustment is made |
| Yeka | 8 | Yeka | 08 | |
| Yeka | 9 | Yeka | 09 | partially added from W.5 |
| Yeka | 10 | Yeka | 10 | partially added from W.5 |

| የተሻሻለዉ ስያሜ | | ነባሩ የ2011 ስያሜ /አዋጅ ቁጥር 64/2011/ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| ክፍለ ከተማ | ወረዳ | የ2011 ክፍለ ከተማ | የ2011 ወረዳ | |
| የካ | 11 | የካ | 11 | የአከላለል ማሻሻያ የተደረገበት |
| የካ | 12 | የካ | 12 | የአከላለል ማሻሻያ የተደረገበት |
| ጉለሌ | 1 | ጉለሌ | 01 | የአከላለል ማሻሻያ የተደረገበት |
| ጉለሌ | 2 | ጉለሌ | 02 | ከወ.1 በከፊል የተጨመረበት |
| ጉለሌ | 3 | ጉለሌ | 03 | ከወ-1 እና ወ-6 በከፍል የተጨመረበት |
| ጉለሌ | 4 | ጉለሌ | 04 እና 05 | ከወ.5 በከፊል የተጨመረበት |
| ጉለሌ | 6 | ጉለሌ | 05 እና 06 | ከወ.5 በከፊል የተጨመረበት |
| ጉለሌ | 7 | ጉለሌ | 07 | |
| ጉለሌ | 8 | ጉለሌ | 08 | |
| ጉለሌ | 9 | ጉለሌ | 09 | |
| ጉለሌ | 10 | ጉለሌ | 10 | |
| ጉለሌ | 5 | ኮልፌ ቀራኒዮ | 15 | ለማመጣጠን ከኮልፌ ቀራኒዮ ሙሉዉ ወረዳ የተወሰደ |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 1 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 01 | ከወ.1 ተከፍሎ እና ከወ.2 በከፊል ተጨምሮ አዲስ የተቋቋመ |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 2 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 02 | ለሁለት ተከፍሎ የተቋቋመ |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 5 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 05 | |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 6 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 06 | |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 7 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 07 | |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 8 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 08 | የወሰን ማሻሻያ የተደረገበት |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 9 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 09 | ከአቃቂ ወ.6 በመጠኑ ተጨምሮ የወሰን ማሻሻያ የተደረገበት |


| Revised Name | | Existing Name in 2019 (Proc. No. 64/2019) | | Remark |
|---|---|---|---|---|
| Sub-City | Woreda | Name of the Sub-City in | Name of the 'Woreda' in 2019 | |
| Yeka | 11 | Yeka | 11 | demarcation adjustment is made |
| Yeka | 12 | Yeka | 12 | demarcation adjustment is made |
| Gullele | 1 | Gullele | 01 | demarcation adjustment is made |
| Gullele | 2 | Gullele | 02 | partially added from W.2 |
| Gullele | 3 | Gullele | 03 | partially added from W.1 and W.6 |
| Gullele | 4 | Gullele | 04 and 05 | partially added from W.5 |
| Gullele | 6 | Gullele | 05 and 06 | partially added from W.5 |
| Gullele | 7 | Gullele | 07 | |
| Gullele | 8 | Gullele | 08 | |
| Gullele | 9 | Gullele | 09 | |
| Gullele | 10 | Gullele | 10 | |
| Gullele | 5 | Kolfe Keraniyo | 15 | the whole woreda is taken from Kolife Keraniyo to balance |
| Nifas Silik Lafto | 1 | Nifas Silik Lafto | 01 | divided from W.1 and partially added from W.2 and newly established |
| Nifas Silik Lafto | 2 | Nifas Silik Lafto | 02 | divided into two and established |
| Nifas Silik Lafto | 5 | Nifas Silik Lafto | 05 | |
| Nifas Silik Lafto | 6 | Nifas Silik Lafto | 06 | |
| Nifas Silik Lafto | 7 | Nifas Silik Lafto | 07 | |
| Nifas Silik Lafto | 8 | Nifas Silik Lafto | 08 | boundary improvement is made |
| Nifas Silik Lafto | 9 | Nifas Silik Lafto | 09 | slightly added from Akakki W.6 and boundary improvement is made |

| የተሻሻለዉ ስያሜ | | ነባሩ የ2011 ስያሜ /አዋጅ ቁጥር 64/2011/ | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| ክፍለ ከተማ | ወረዳ | የ2011 ክፍለ ከተማ | የ2011 ወረዳ | |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 10 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 10 | |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 11 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 11 | ለወ.12 በከፊል 214.5 ሄ.ር በመስጠት ማሻሻያ የተደረገበት |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 12 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 12 | ከወ.11 በከፊል 214.5 ሄ.ር ተጨምሮ ማሻሻያ የተደረገበት |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 13 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 2 | ለሁለት ተከፍሎ የተቋቋመ |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 14 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 01 | ከወ.1 ተከፍሎ አዲስ የተቋቋመ |
| ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 15 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ | 01 | ከወ.1 ተከፍሎ አዲስ የተቋቋመ |
| አቃቂ ቃሊቲ | 2 | አቃቂ ቃሊቲ | 02 | ለሁለት የተከፈለና ከ ወ.1 በከፊል የተጨመረበት |
| አቃቂ ቃሊቲ | 3 | አቃቂ ቃሊቲ | 03 | ከወ1 እና ከወ.2 በከፊል የተጨመረበት |
| አቃቂ ቃሊቲ | 4 | አቃቂ ቃሊቲ | 04 | ከወ.7 በከፊል የተጨመረበት |
| አቃቂ ቃሊቲ | 5 | አቃቂ ቃሊቲ | 05 | ከወ 7 እና ከወ.8 በከፊል የተጨመረበት |
| አቃቂ ቃሊቲ | 6 | አቃቂ ቃሊቲ | 06 | ከን/ስ/ላ ወ-9 እና ከአቃቂ ከወ.5 በከፊል የተጨመረበት |
| አቃቂ ቃሊቲ | 7 | አቃቂ ቃሊቲ | 07 | ከወ.4፣ ወ.5 እና ወ.8 በከፊል የተጨመረበት |
| አቃቂ ቃሊቲ | 8 | አቃቂ ቃሊቲ | 08 | ከወ.5 እና ወ.7 በከፊል የተጨመረበት |
| አቃቂ ቃሊቲ | 1 | አቃቂ ቃሊቲ | 01 | ከወ.9 በከፊል የተጨምረበት |
| አቃቂ ቃሊቲ | 13 | አቃቂ ቃሊቲ | 09 | ከወ-2 ተከፍሎ፣ ከወ.9 እና ወ-9 በከፍል የተጨመረበት |
| አቃቂ ቃሊቲ | 12 | አቃቂ ቃሊቲ | 9 እና 11 | ከቀድሞ ወ-9 እና ከወ-11 በከፍል የተጨመረበት |
| አቃቂ ቃሊቲ | 10 | አቃቂ ቃሊቲ | 9 እና 11 | ከቀድሞ ወረዳ 9 እና ከወ-11 ተከፍለዉ የተቋቋመ |
| አቃቂ ቃሊቲ | 9 | አቃቂ ቃሊቲ | 9 እና 10 | የቀድሞ ወ-9 በከፊል እና ከወ-10 ጋር ተቀላቅለዉ የተቋቋመ |
| አቃቂ ቃሊቲ | 11 | አቃቂ ቃሊቲ | 11 | ከቀድሞ ወ-9 በከፊል ተጨምሮ ተከፍለዉ የተቋቋመ |

| Revised Name | | Existing Name in 2019 (Proc. No. 64/2019) | | Remark |
|---|---|---|---|---|
| Sub-City | Woreda | Name of the Sub-City in | Name of the 'Woreda' in 2019 | |
| Nifas Silik Lafto | 10 | Nifas Silik Lafto | 10 | |
| Nifas Silik Lafto | 11 | Nifas Silik Lafto | 11 | partially provide 214.5 hectares to W.12 and demarcation adjustment is made |
| Nifas Silik Lafto | 12 | Nifas Silik Lafto | 12 | partially added 214.5 hectares to W.11 and demarcation adjustment is made |
| Nifas Silik Lafto | 13 | Nifas Silik Lafto | 2 | divided into two and established |
| Nifas Silik Lafto | 14 | Nifas Silik Lafto | 01 | divided from W.1 and newly established |
| Nifas Silik Lafto | 15 | Nifas Silik Lafto | 01 | divided from W.1 and newly established |
| Akaki Kaliti | 2 | Akaki Kaliti | 02 | divided into two and partially added from W.1 |
| Akaki Kaliti | 3 | Akaki Kaliti | 03 | partially added from W.1 and W.2 |
| Akaki Kaliti | 4 | Akaki Kaliti | 04 | partially added from W.7 |
| Akaki Kaliti | 5 | Akaki Kaliti | 05 | partially added from W.7 and W.8 |
| Akaki Kaliti | 6 | Akaki Kaliti | 06 | partially added from Nifas Silik Lafto W.9 and Akaki W.5 |
| Akaki Kaliti | 7 | Akaki Kaliti | 07 | partially added from W.4, W.5 and W.8 |
| Akaki Kaliti | 8 | Akaki Kaliti | 08 | partially added from W.5 and W.7 |
| Akaki Kaliti | 1 | Akaki Kaliti | 01 | partially added from W.9 |
| Akaki Kaliti | 13 | Akaki Kaliti | 09 | divided from W.2; partially added from W.9 |
| Akaki Kaliti | 12 | Akaki Kaliti | 9 and 11 | partially added from the former W.9 and W.11 |
| Akaki Kaliti | 10 | Akaki Kaliti | 9 and 11 | divided from the former W.9 and W.11; and established |
| Akaki Kaliti | 9 | Akaki Kaliti | 9 and 10 | partial part of the former W.9 and merged with W.10 and established |
| Akaki Kaliti | 11 | Akaki Kaliti | 11 | partially added from the former W.9 and established by division |

## አባሪ 2


## የከተማ አስተዳደራዊ መዋቅር



**Annex 2**


## Administrative Structure of the City


### 11 Sub-Cities and 120 'Woredas'





# አባሪ-3

## የክፍለ ከተሞች ማስተካከያ


| ተ.ቁ | ክፍለ ከተሞች | ግራፊክ መግለጫ | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| 1 | አራዳ-የካ |  | • ጃን ሜዳ 43.5 ሄ/ር ከየካ ወ-4 ወደ ወደ አራዳ ወ-6፣ ሚኒልክ አካባቢ 17.4 ሄ/ር ከአራዳ ወ-7 ወደ የካ ወ-4 እና አዋሬ አካባቢ 7.4 ሄ/ር ከየካ ወ-7 ወደ አራዳ ወ-7 የተሠራዉን መንገዱን ተከትለዉ ማስተካከያ ተደርጓል፡፡ |
| 2 | አራዳ-ልደታ-ቂርቆስ |  | አራዳ ወ.01፣ ልደታ ወ.06 እና ቂርቆስ ወ.07 መካከል ያለውን አከላለል ዋና መንገዶችን ተከትሎ እንዲሄድ ማድረግ<br>1. 16 ሄ/ር የሸራተን ማስፋፊያ ተብሎ የሚታወቀው ቦታ ከቂርቆስ ወ.07 ወደ አራዳ<br>2. 2.95 ሄ/ር ከቂርቆስ ወ.07 ወደ ልደታ ወ.08<br>3. 4.41 ሄ/ር ከአራዳ ወ.01 ወደ ልደታ ወ.08<br>4. 1.4 ሄ/ር አምባሳደር ፓርክ ከአራዳ ወ.01 እና 0.85 ሄ/ር ከልደታ ወ.08 ወደ ቂርቆስ ወ.07 |


| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 | ቂርቆስ-ቦሌ |  | • ወረዳዎችን ተመጣጣኝ ስፋት ከመስጠት ጋር ተያይዞ 29.7ሄ/ር ቦታ ከቦሌ ወ.04 ወደ ቂርቆስ ወ.01 እንዲቀላቀል ተደርጓል፡፡ |
| 4 | ኮልፌ-ንፋስ ስልክ ላፍቶ |  | ከረጲ ተራራ በስተ ደቡብ ምዕራብ በኩል ያለውን አከላለል መንገድ ይዞ እንዲሄድ ማድረግ እና ጀሞ 3 የኮንደሚኒየም ሰፈርን በመንገድ እንዲሄድ ማድረግና ጀሞ 2 የኮንደሚኒየም ሰፈር ለሁለት የሚከፈለዉ በ120 ሜትር መንገድ ሙሉ በሙሉ ወደ ኮልፌ ቀራንዮ ማካተት፡፡<br>1. 145.5 ሄ/ር ከን.ስ.ላፍቶ ወ.01 ወደ ኮልፌ ቀራንዮ ወ.02 እንዲካተት ተደርጓል፡፡<br>2. 21 ሄ/ር ከኮልፌ ቀራንዮ ወ.01 ወደ ን.ስ.ላፍቶ ወ.02 እንዲካተት ተደርጓል፡፡<br>3. 40.5 ሄ/ር ከን.ስ.ላፍቶ ወ.02 ወደ ኮልፌ ቀራንዮ ወ.01 እንዲካተት ተደርጓል፡፡<br>4. 27 ሄ/ር ወደ 14 ይዞታዎች ከኮልፌ ቀራንዮ ወ.05 ወደ ን.ስ.ላፍቶ ወ.03 እንዲካተት ተደርጓል፡፡ |
| 5 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ እና አቃቂ ቃሊቲ |  | 33.3 ሄ/ር ከአቃቂ ቃሊቲ ወ.6 ወደ ን.ስ.ላፍቶ ወ.09 እና ን.ስ.ላፍቶ ወ.09 ወደ አቃቂ ቃሊቲ ወ.6 1.96 ሄ/ር እንዲካተት ተደርጓል፡፡ |



| | | | |
|---|---|---|---|
| 6 | ኮልፌ ቀራንዮ- ጉለሌ |   | ክፍለ ከተሞችን ተመጣጣኝ ስፋት ከመስጠት እና የክፍለ ከተማ ማዕከል ቅርበት ከኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 15 ወደ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳዉ እንዳለ እንዲቀላቀል ተደርጓል፡፡ |
| 7 | ኮልፌ ቀራንዮ- አዲስ ከተማ |   | ክፍለ ከተሞችን ተመጣጣኝ ስፋት ከመስጠት እና የክፍለ ከተማ ማዕከል ቅርበት ከኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11፣ 12፣ 13፣ እና 14 ወደ አዲስ ከተማ ክፍለከተማ ወረዳዎቹ በሙሉ እንዲቀላቀል ተደርጓል፡፡ |
| 8 | ጉለሌ- የካ |   | መሠረተ ልማትን ተከትሎ ከየካ 04 ወደ ጉለሌ 03 ማስተካከያ ተደርጓል፡፡ |

## Annex 3

## Adjustment of Sub-Cities



| No | Sub-Cities | Graphic Description | Explanation |
|---|---|---|---|
| 1 | Arada-Yeka |  | Jan Meda 43.5 hectares from Yeka W.4 to Arada W.6; Minilik area 17.5 hectares from Arada W.7 to yeka W.4 and Aware area 7.4 hectares from Yeka W.7 to Arada W.7 adjustments have been made following the constructed road |
| 2 | Arada-Lideta-Kirkos |  | Making the demarcation between Arada W.01, Lideta W.06 and Kirkos W.07 to follow main roads:<br>1. 16 hectares, known as the Sheraton expansion from Kirkos W.07 to Arada;<br>2. 2.95 hectares from Kirkos W.07 to Lideta W.08;<br>3. 4.41 hectares from Arada W.01 to Lideta W.08;<br>4. 1.4 hectares of Ambassador Park from Arada W.01 and 0.85 hectares from Lideta W.08 to Kirkos W.07 |




| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 | Kirkos-Bole |   | An area of 29.7 hectares from Bole W.04 is included to Kirkos W.01 with regard to providing a balanced size for the woredas. |
| 4 | Kolife Keraniyo-Nifas Silik Lafto |   | Make the demarcation towards the South-West of Repi Mountain to follow the road; and make the Jemo 3 condominium village to follow the road; and to fully include the 120 meters long road that divides the Jemo 2 condominium village to Kolife Keraniyo.<br>1. 145.5 hectares from Nifas Silik Lafto W.01 is included to Kolife Keraniyo W.02<br>2. 21 hectares from Kolife Keraniyo W.01 is included to Nifas Silik Lafto W.02<br>3. 40.5 hectares from Nifas Silik Lafto W.02 is included to Kolife Keraniyo W.01<br>4. 27 hectares of 14 premises from Kolife Keraniyo W.05 is included to Nifas SilikLafto W.03 |
| 5 | Nifas Silik Lafto and Akaki Kaliti |   | 33.3 hectares from Akaki Kaliti W.6 is included to Nifas Silik Lafto W.09; and 1.96 hectares from Nifas Silik Lafto W.09 is included to Akaki KAliti W.6 |





| | | | |
|---|---|---|---|
| 6 | Kolife Keraniyo-Gullele |  | W.15 from Kolife Keraniyo sub-city is totally included to Gullele sub-city in order to provide a balanced size for sub-cities and considering proximity to the center |
| 7 | Kolife Keraniyo-Addis Ketema |  | W.11, W.12, W.13 and W.14 from Kolife Keraniyo sub-city are totally included to Addis Ketema sub-city inorder to provide a balanced size for the sub-cities and considering proximity to the center |
| 8 | Gullele-Yeka |  | Adjustment is made from Yeka W.04 to Gullele W.03 following infrastructures |







## አባሪ-4




### የወረዳ ማስተካከያ



| ተ.ቁ. | በክፍለ ከተማ ደረጃ | ዝርዝር ግራፊክ መግለጫ | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| 1. | **ቂርቆስ**<br> |  | -ወ-1 ለቂርቆስ ወ-8 8.7 ሄ.ር በመስጠት፣ ከቂርቆስ ወ-8 3.02ሄ/ር እና ከቦሌ ወ-4 29.71ሄ/ር በማካተት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-2 ለወ-9 3.51 ሄ/ር እና ለወ-3 19.93ሄ/ር በመስጠት፣ከወ-9 2.38 ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-3 ከወ-9 19.93ሄ/ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-4 ለወ-11 43.37 ሄ.ር በመስጠት፣ ከወ-5 45.22 ሄ.ር በማካተት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-5 ወ-5 በክፍል እና ወ-6 በክፍል በአንድ ላይ የተቀላቀለ፡፡<br>-ወ-7 ለአራዳ ወ-9 16.5 ሄ.ር፣ ለልደታ ወ-8 2.95 ሄ.ር እና ለቂርቆስ ወ-10 44.89 ሄ.ር በመስጠትና ፣ ከወ-6 8.06 ሄ.ር፣ ከወ-9 4.71 ሄ.ር፣ ከልደታ ወ-8 0.84 ሄ.ር እና ከአራዳ ወ-1 1.40 ሄ.ር አካቶ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-8 ለወ-1 3.02 ሄ/ር በመስጠት እና ከወ-1 8.79 ሄ.ር ማካተት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-9 ለወ-2 2.3 ሄ/ር እና ለወ-7 4.7 ሄ.ር በመስጠት፣ ከወ-2 3.5 ሄ.ር በማካተት የተስተካከለ፡፡<br><br>-ወ-10 ለወ-11 24.33 ሄ.ር በመስጠት፣ ከወ-6 9.27 ሄ.ር፣ ከወ-7 44.89 ሄ.ር እና ከቀድሞ ወ-11 24.56 ሄ.ር አካቶ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-11 ለወ-10 24.56 ሄ.ር በመስጠት፣ ከወ-4 43.37 ሄ.ር እና ከቀድሞ ወ-10 24.33 ሄ.ር አካቶ የተስተካከለ፡፡ |





| | | | |
|---|---|---|---|
| | |  | |
| **2.** | **ልደታ**<br> |  | • ወ-1 ለወ-10 13.27 ሄ/ር በመስጠት የተስተካከለ፡፡<br>• ወ-3 ከቀድሞ ወ-04 51.77 ሄ/ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>• ወ-9 ለወረዳ 5 14.01 ሄ/ር በመስጠት፣ ከወረዳ 4 36.21 ሄ/ር በመዉሰድ የተቋቋመ፡፡<br>• ወ-5 ወ-5 እና ወ-6 ተቀላቅለዉ ከወ-9 14ሄ/ር በመዉሰድ የተቋቋመ፡፡<br>• ወ-7 ወ-7 እና ወ-8 ተቀላቅለዉ ከአራዳ ወ-1 4.4ሄ/ር እና ከቂርቆስ ወ-7 2.95ሄ/ር በመዉሰድ የተቋቋመ፡፡<br>• ወ-10 ከወ-1 13.27 ሄ/ር በመዉሰድ የተቋቋመ፡፡<br>• ወ-4 ከንፋስ ስልክ ላፍቶ የተወሰደ<br>• ወ-6- ከኮልፌ ቀራንዮ ወ-5 27 ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለና ከንፋስ ስልክ ላፍቶ ወ-3 ተካፍሎ የተተቋቋመ<br>• ወ-8 ከንፋስ ስልክ ላፍቶ ወ-3 ተወስዶና ተካፍሎ የተተቋቋመ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **3.** | **አራዳ**<br> |  | -ወ-1 ለልደታ ወ-8 4.41 ሄ.ር እና ለቂርቆስ ወ-7 1.40 ሄ.ር በመስጠት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-2 ወ-2 እና ወ-3 ተቀላቅለዉ ከወ-5 14.28 ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-5 ወ.5 ለወ-2 14.28 ሄ/ር በመስጠት ቀሪዉ ከወ.10 ጋርበአንድየተጠቃለለ<br>-ወ-6 ከየካ ወ-4 43.54 ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለ ፡፡<br>-ወ-7 ለየካ ወ-4 17.42 ሄ.ር፣ለአረዳ ወ-8 12.33 ሄ.ር በመስጠት፣ከየካ ወ-6 7.45 ሄ.ር ፣ከአራዳ ወ-8 0.66 ሄ.ር እና ከወ-9 0.33ሄ.ር በማካተት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ 8 ለወ-7 0.66 ሄ.ር እና ለወ-9 25.1 ሄ.ር በመስጠት፣ ከወ-7 12.33 ሄ.ር በማካተት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-9 ለ7 0.33ሄ.ር በመስጠት፣ ከቂርቆስ ወ.7 16.5 ሄ.ር እና ከአራዳ ወ-8 25.18 ሄ.ር በማካተት የተስተካከለ፡፡ |
| **4.** | **ጉለሌ**<br> |  | -ወ-1 ለወ-2 0.73 ሄ.ር እና ለወ-3 15.52 ሄ.ር በመስጠት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-2 ለየካ ወ-4 1.24 ሄ.ር በመስጠት፣ ከጉለሌ ወ-1 0.73 ሄ.ር በማካተት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-3 ከወ-1 15.52 ሄ.ር እና ከወ-6 1.99 ሄ.ር በማካተት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-4 ከወ-5 83.6 ሄ.ር በማካተት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-6 ለወ-3 1.99 ሄ.ር በመስጠት፣ ከወ-5 53.2 ሄ.ር በማካተት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-5 ለማመጣጠን ከኮልፌ ቀራንዮ ወረዳ 15 ሙሉዉን የተወሰደ፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5. | **አዲስ ከተማ**<br> |  <br><br> | ➢ ወ-2 ለወ-4 1.72 ሄ.ር በመስጠት፤ ወ-2 እና ወ-3 ተቀላቅለዉ የተደራጀ፡፡<br>➢ ወ-4 ከወ-3 1.72 ሄ.ር ሄ.ር በማካተት የተስተካከለ፡፡<br>➢ ወ-5 ለወ-6 9 ሄ.ር በመስጠት በመስጠት የተስተካከለ፡፡<br>➢ ወ-6 ወ-7 11.4 ሄ.ር ለወ-9 በመስጠት፤ ከወ-5 9 ሄ.ር በማካተት ወ-6 እና ወ-7 ተቀላቅለዉ የተደራጀ፡፡<br>➢ ወ-9 ከቀድሞ ወ-7 11.4 ሄ.ር ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>➢ ወ-11 ቀድሞ በኮ/ቀ ስር የነበረና መንገድን ተከትለዉ ኮልፌ ወ-8 ጋር የተስተካከለ፡፡<br>➢ ወ-12 ቀድሞ በኮ/ቀ ስር የነበረና ከወረዳ 13 128.9 ሄ.ር እና ከወ-11 4.3 ሄ.ር በማካተት የተስተካከለ፡፡<br>➢ ወ-13 ቀድሞ በኮ/ቀ ስር የነበረና ለመመጣጠን ለወ-12 128.9 ሄ.ር ሄ.ር በመስጠት ቀሪዉ በወረዳነት ቀጠለ፡፡<br>➢ ወ-14 ቀድሞ በኮ/ቀ ስር የነበረ፡፡ |
| 6. | **ኮልፌ ቀራንዮ**<br> |  <br>  | -ወ-1 ለን/ስ/ላ/ክ/ከ ለወ-2 21.8 ሄ.ር በመስጠት፤ ከን/ስ/ላ ወ-2 34.5 ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-2 ከን/ስ/ላ ወ-1 145.5 ሄ.ር ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-3 ለወ-7 79.42 ሄ.ር በመስጠት ለሁለት ተከፍሎ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-5 ለን/ስ/ላ/ክ/ከ ወ-3 27 ሄ.ር በመስጠትና ተስተካክለዉ የተደራጀ፡፡<br>-ወ-7 ከወ.3 79.42 ሄ.ር ተጨምሮ የወሰን ማሻሻያ የተደረገበት፡፡<br>-ወ-8 ለቀድሞ 11 20.38 ሄ.ር በመስጠት እና ከቀድሞ ወ.11 11.88 ሄ.ር በመዉሰድ የወሰን ማሻሻያ የተደረገበት፡፡<br>-ወ-9 ለ10 42.9 ሄ.ር በመስጠት የወሰን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ማሻሻያ የተደረገበት፡፡<br>-ወ-11 ከወረዳ 3 ተከፍሎ አዲስ የተቋቋመ፡፡ |
| **7.** | **ንፋስ ስልክ ላፍቶ**<br> |  | -ወ-1 ለን/ስ/ላ ወ-2 0.79 ሄ.ር እና ለቀራንዮ ወ-2 145.5 ሄ.ር በመስጠት፤ ከን/ስ/ላ ወ-2 49 ሄ.ር በመዉሰድ ለሶስት ተከፍሎ የተቋቋመ፡፡<br>ወ-2 ለኮልፌ ቀራንዮ ወ-1 34.5 ሄ.ር ፣ ለን/ስ/ላ ወ-1 49 ሄ.ር በመስጠት፤ ከቀራንዮ ወ-1 21.8 ሄ.ር ፣ ወ-1 0.79 ሄ.ር እና ወ-12 0.12 ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-8 ለወ-9 1.7 ሄ.ር በመስጠት፤ ከወ-9 4.53 ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-9 ለወ-8 4.53 ሄ.ር በመስጠት፤ ከወ-8 1.7 ሄ.ር እና ከቀድሞ አቃቂ ቃሊት ወ-6 54.51 ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-11 ለወ-2 14.5 ሄ.ር በመስጠት የወሰን ማሻሻያ የተደረገበት፡፡<br>-ወ-12 ለወ-2 0.12 ሄ.ር በመስጠት፤ ከወ-11 14.5 ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-13 ከወ.1 ተከፍሎ አዲስ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-14 ከወ.1 ተከፍሎ አዲስ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-15 ከወ.1 ተከፍሎ አዲስ የተቋቋመ፡፡ |
| **8.** | **ቦሌ**<br> |  | .ወ-1 ከወ-13 34.7 ሄ.ር እና ከወ-12 353.4 ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>.ወ-3 ለወ-4 75.6 ሄ.ር እና ለወ-5 3.2 ሄ.ር በመስጠት የተስተካከለ፡፡<br>.ወ-4 ለቂርቆስ ወ-1 29.71ሄ/ር እና ለወ-4 42.1 ሄ.ር በመስጠት፤ከወ-3 152.67 ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-5 ከወ-4 42.1 ሄ.ር እና ከወ-3 3.2 ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-13 ለወ-1 34.7 ሄ.ር በመስጠት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-11- ለወ-9 19.3 ሄ.ር በመስጠት፤ከ ወ-9 24.1 ሄ.ር በመዉሰድ ለሁለት ተከፍሎ አንደኛዉን ለአዲሱ ክ/ከተማ በመስጠት የተቋቋመ<br>-ወ-12- ለወ-1 353.4 ሄ.ር በመስጠት የተስተካከለ፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | |  | |
| 9. | **ለሚ ኩራ**<br><br> | <br> | -ወ-14፡- ከየካ ወ-12 ለሁለት ተካፍሎና ከየካ ወ-13 44.3 ሄ.ር በማካተት በአዲሱ ክ/ከተማ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-13፡- ከየካ ወ-11 128.65 ሂ/ር በመዉሰድ እና ከወ-13 ለሁለት ተካፍሎ በአዲስ ክ/ከተማ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-2፡- ከየካ ወ-13 ተካፍሎ በአዲስ ክ/ከተማ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-3፡- ከቦሌ ወ.10 ተከፍሎ አዲስ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-4፡- ከቦሌ ወ.10 ተከፍሎ አዲስ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-5፡- ከቦሌ ወ.10 ተከፍሎ አዲስ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-10፡- ከቦሌ ወ.10 ተከፍሎ አዲስ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-09፡- ለወ-11 24.1 ሄ.ር በመስጠት፣ ከ ወ-11 19.3 ሄ.ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-7፡- ከቀድሞ ቦሌ ወ-11 ለሁለት ተከፍሎ በአዲሱ ክ/ከተማ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-8፡- ከቀድሞ ቦሌ ወ-8 የነበረና በአዲሱ ክ/ከተማ የተቋቋመ፡፡ |
| 10. | **የካ** |  | -የካ ወ-4፡- ለአራዳ ወ-6 43.5 ሂ/ር፣ ከጉለሌ ወ-2 1.24ሂ/ር እና ለአረዳ 07 17.4 ሂ/ር በመዉሰድ<br>-ወ-5፡- ለወ-9 14.3 ሂ/ር፣ ለወ-10 56.17 ሂ/ር በመስጠት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-6፡- ከወ-7 19.8 ሂ/ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-7፡- ለአራዳ ወ-7 7.4 ሂ/ር እና ለየካ ወ-6 19.8 ሂ/ር በመስጠት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-9፡- ከወ-5 14.3 ሂ/ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-10፡- ከወ-5 56.17 ሂ/ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| |  |  | -ወ-11፡- ለቀድሞ የካ ወ-13 ከወ-5 128.65 ሄ/ር በመስጠት የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-12፡- ለሁለት ተከፍሎ አንዱን ለአዲሱ ክ/ከተማ ሥር በመስጠት የተቋቋመ:: |
| **11.** | **አቃቂ ቃሊቲ**<br> |  | -ወ-02 ለወ-03 48.14 ሄ/ር በመስጠት እና ከወ-1 52.54 ሄ/ር በመዉሰድ ለሁለት ተከፍለዉ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-03 ለወ-1 0.79 ሄ/ር በመስጠት፤ ከወ-1 118.9 ሄ/ር እና ከወ-02 48.14 ሄ/ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-04 ለወ-07 163.35 ሄ/ር በመስጠት እና ከወ-07 17.18 ሄ/ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-05 ለወ-6 47.9ሄ.ር፣ ለወ-7 8.75 ሄ/ር እና ለወ-8 2.34 ሄ/ር በመስጠት፤ ከወ-7 10.66 ሄ/ር እና ከወ-8 12.38 ሄ/ር በመዉሰድ የተስተካከለ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-6 ከን/ስ/ላ/ክ/ከ ወ-9 1.75 ሄ.ር ከአቃቂ ቃሊት ከወ-5 47.9 ሄ.ር በመዉሰድ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-07 ለወ-4 17.13 ሄ/ር፣ ለወ-5 10.66ሄ/ር ፣ለወ-8 10.32 ሄ/ር በመስጠት፤ከወ-04 163.35 ሄ/ር፤ ከወ-5 8.75 ሄ/ር፣ ከወ-8 19.97 ሄ/ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-08 ለወ-5 12.38 ሄ/ር፣ ለወ-7 19.7ሄ/ር በመስጠት፤ ከወ-5 2.34 ሄ/ር፤ ከወ-7 10.32 በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-1 ለወ-2 52.54 ሄ/ር፣ ለወ-3 118.93 ሄ/ር፣ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | አዲስ ከወ-2 ተከፍለዉ ለተደራጀዉ (ወ-13) 104.32 ሄ/ር እና ለወ-9 44.26 ሄ/ር በመስጠት፤ ከወ-3 1.79 ሄ/ር እና ከወ-09 385.43 ሄ/ር በመዉሰድ የተስተካከለ፡፡<br>-ወ-13 ቀድሞ ወረዳ 1-104.32 ሄ/ር፣ ከወ-9 253.49 ሄ/ር በመዉስደ ከቀድሞ ወ-2 ተከፍለዉ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-12 ቀድሞ ወረዳ 11 261.71 ሄ/ር በመዉስደ ከቀድሞ ወ-9 ተከፍለዉ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-10 ቀድሞ ከወ-9 እና ከወ-11 ተከፍለዉ የተቋቋመ፡፡<br>-ወ-9 የቀድሞ ወ-9 በከፊል እና ከወ-10 ጋር ተቀላቅለዉ የተቋቋመ<br>-ወ-11 አዲስ ለተቋቋመ ወ-3 261.71 ሄ/ር በመስጠት እና ከቀድሞ ወ-9 28.31 ሄ/ር በመዉሰድ ተከፍለዉ የተሰተካከለ፡፡ |